በትምህርት ቤት አውቶቡስ ስለመጓዝ ፡ የያንዳንዱ ተማሪ ተጓዥ ግዴታዎች።
እያንዳንዱ ተማሪ አካባቢውን ከሚሸፍን አውቶቡስ መውረድ ወይም መውጣት የሚችለው ከተመደበለት የአውቶቡስ ማቆሚያ ብቻ ነው።

1. በአውቶብሱ ላይ በጠዋት መውጣት። የሁሉም ክፍሎች ተማሪዎች በአውቶቡስ ማቆሚያ ላይ ከተመደበላቸው መሄጃ ሰአት 5 ደቂቃዎች በፊት መገኘት አለባቸው። ይህም የአውቶብሱ ሾፌር አውቶብሱ ማቆሚያው ጋር ሲቃረብ ተማሪውን እንዲያየው በቂ ጊዜ ይሰጠዋል።

   ሀ. ተማሪዎች መረዳት ያለባቸው ነገሮች ቢኖር አውቶብሱ ካመለጣቸው፣ አውቶብሱን ማሳደድ የለባቸውም፤ ሾፌሩ የሚያየው ወደ ትራፊክ እንጂ ወደ አውቶብሱ የበር ጎን ስላልሆነ፣ ይህ በጣም አደገኛ ወቅት ነው።

   ለ. አውቶብሱ ሲደርስ ከመንገድ ይራቁ። አውቶብሱ ሙሉ ለሙሉ ሲቆም እና በሩ ሲከፈት፣ ተማሪዎች የእጅ መደገፊያውን በመጠቀም ወደ አውቶብሱ ገብተው ወደ ተመደበላቸው መቀመጫ በፍጥነት ይሂዱ።

1. እያንዳንዱ ተማሪ የተመደበለት መቀመጫ ይኖረዋል (ምንም እንኳን በጊዜያዊነት ቢሆንም) ። ሾፌሩ ሁሉም ተማሪዎች እስኪቀመጡ ድረስ አውቶብሱን ላያንቀሳቅስ ይችላል።

   ሀ. ተማሪዎች በተመደበላቸው መቀመጫ ላይ በስነ ስርአት ልክ በሚከተለው መልኩ መቀመጥ አለባቸው፣ “በመቀመጫዎ ተቀምጠው እግሮችዎ በወለሉ ላይ፣ ከመተላለፊያው ውጪ”

   ለ. ተማሪዎች በወለሉ ላይ መቀመጥ፣ በመተላለፊያው ላይ መቀመጥ ወይም መቆም፣ ወይም ከሾፌሩ ጎን ወይም አካባቢ መቀመጥ አይፈቀድላቸውም።

1. ከሰኣት በሁዋላ ወደ አውቶቡሱ ላይ መውጣት። እያንዳንዱ ካምፓስ ልዩ የአውቶቡስ መጫኛ ቦታ እና አውቶቡስ ተጠቃሚ ተማሪዎችን የሚለቅበት አሰራሮች አሉት። ተማሪዎች የተመደበላቸውን የአካባቢያቸውን አውቶቡስ እንዲጠቀሙ ሲጠበቅ ይህም ትምህርት ቤት ወዳሰናዳው የክንውን አውቶቡስ እንዲሄዱ ካልተፈቀደ በስተቀር ነው።

   ሀ. አውቶብሱ ላይ ሲገባ፣ ሚዛንን ለመጠበቅ እጀታውን ይጠቀሙ፤ አውቶብሱ ላይ ገብተው ወደተመደበልዎ መቀመጫ ይሂዱ። ተመቻችተው ጉዞውን በደስታ ለመቀጠል ይዘጋጁ።

   ለ. ተማሪው ከሱ ወይም ከሱዋ ጋር ወደቤት የሚሄድ ካለ፣ ጉብኚው ተማሪ ከወላጅ ወይም አሳዳጊ የተጻፈ በካምፓሱ አስተዳዳሪ የተሰጠ የጊዜያዊ የአውቶቡስ ማለፊያ ሊኖረው ይገባል። በመጫኛ ስፍራ ያለው የካምፓሱ አስተዳዳሪ ሁኔታዎቹን አይቶ ተማሪው ወደ ውስጥ እንዲገባ ወይም <u>ጊዜያዊ የአውቶቡስ ማለፊያ</u> (በቦታው ላይ)ወደ አውቶብሱ እንዲሄድ ማድረግ ይችላል።

   ሐ. በከሰኣት በሁዋላው ጉዞ፣ ተማሪው ከተመደበበት መሳፈሪያ ቦታ ውጪ ቢፈልግ እና የወላጅ ወይም የትምህርት ቤት ፍቃድ ከሌለው፣ ሾፌሩ የመጓጓዣ ሰራተኞች ጋር ይገናኛል። ተማሪው ያለፍቃድ ከዚህ ውጪ መሆን አይችልም።

i. ተማሪው በመደበኛው መውረጃ ቦታው ላይ ከአውቶብሱ አልወርድም ካለ (ወይም አውቶብሱ ቦታውን ካለፈው)፣ ካምፓሱን ለማብራሪያ እናገኛለን ይህም ሾፌሩ ተማሪውን በአውቶብሱ ውስጥ ያቆያል።

i. ተማሪው በአውቶብሱ ከቆየ፣ ያ ተማሪ በአውቶብሱ ፊት ለፊት ጉዞው እስኪያልቅ ድረስ ጸጥ ብለው እንዲቀመጡ ይጠበቃል፤ በዚህም ወቅት ተማሪው ወደ ካምፓሱ ከወላጁ ጋር ወይም ከህጻናት ጥበቃ

አገልግሎቶተ ጋር ይገናኖል።

1. ተማሪዎች ቁጭ ብለው እንዲቆዩ ሲጠበቅ  ይህም የትምህርት ቤት አውቶብሱ በተመደበላቸው ማቆሚያ ወይም ካምፓስ ሙሉ ለሙሉ ሲቆም ነው።

    ሀ. አውቶብሱ የማቆሚያ ስፍራዎች ሲቃረብ፣ ተማሪው እቃዎቹን ሰብስቦ ለመውረድ መዘጋጀት አለበት።

    ለ. አውቶብሱ ሙሉ ለሙሉ ሲቆም፣ ተማሪው ተነስቶ ወደ አውቶብሱ ፊት በመራመድ የእጅ መደገፊያውን በመጠቀም ወደ ደረጃው መውረድ አለበት።

1. የትምህርት ቤት አውቶብሱን ሲወጡ፣ ተማሪው ቢያንስ 10 ፊት ከመኪናው መራቅ ሲኖርባቸው ይህም ከ "አደጋ ዞኑ" እንዲወጡ ያደርጋል።

    ሀ. ተማሪዎች መንገዱን እንዲያቋርጡ የሚጠበቁት ከትምህርት ቤቱ አውቶቡስ ፊት ለፊት ሲሆን ይህም የቀይ ሙብራቶች ሲበሩ ነው፣ ይህም መጪ ትራፊክ መቆጣጠር ያስችላል።

    ለ. ያለ አውቶቡስ ሾፌሩ ወይም ተቆጣጣሪው ፍቃድ፣ አንድ ተማሪ ከትምህርት ቤት አውቶብሱ ስር በጭራሽ መድረስ የለበትም።

1. ተማሪዎች በቤት ውስጥ ድምጽ ማውራት ሲጠበቅባቸው   ይህም ስርአት ባለው ቋንቋ ሲሆን፣ ይህም የአውቶብሱ ሾፌር ለተማሪዎች ቡድን ወይም ለአንድ ተማሪ ተጓዥ መመሪያ ሲሰጥ ለመስማት እንዲችሉ ነው።

1. ተማሪዎች ከማንኛውም የአውቶቡስ መሳሪያዎች ጋር መጫወት አይፈቀድላቸውም፣ በተለይ ከአደጋ ጊዜ መውጫዎች፣ ወይም ጭንቅላታቸውን ወይም እጆቻቸውን በአውቶብሱ መስኮት ማውጣት አይቻልም።

1. ወላጅ ተማሪያቸው ወደተለየ የአውቶቡስ ማቆሚያ ቦታ በቋሚነት እንዲመደቡ ከፈለጉ፣ ከተማሪ አገልግሎት ቢሮ የቅድሚያ ፈቃድ ማግኘት አለባቸው፤ ማመልከቻዎን በካምፓስዎ ያስገቡ።